የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(አንድነት/United)


# ስለ ሽግግር መንግሥት አስፈላጊነት፣ አመሠራረትና ይዘት፣ በኢሕአፓ (አንድነት) የቀረበ ሠነድ

ጥቅምት ፲፩ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ. ም

October 21, 2016

**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(**አንድነት**/United)

# ስለ ሽግግር መንግሥት አስፈላጊንት፣ አመሠራረትና ይዘት፣ በኢሕአፓ (አንድነት) የቀረበ ሠነድ

## መግቢያ

እኛ ኢትዮጵያውያን ያለጥርጥር የአኩሪ ታሪክና ባህል ባለቤቶች ነን። ሀገራችን በዓለም ውስጥ ቀደምት ከሚባሉት ሀገሮች ውስጥ አንዷ ነች። ሀገራችን የሰው ዘር መገኚያ ከመሆንዋም በላይ ዜጎቿ የራሳችንን ፊደል በመፍጠርና በመጻፍ፣ ዜማን በመቃኘትና በመከየን፣ ማዕድናትን በማንጠርና መገልገያዎችን በመሥራት፣ ሃውልቶችንና ግንቦችን በመገንባት፣ ነፃነታችንን ከባዕዳን ወራሪዎች በታላቅ ገድል ተከላክለን በመጠበቅ፣ ኮርተንና ታፍረን የኖርን ነን። በግብራችን ነው ትልቅነትን የተላበስነው። ከአራት ዋና ዋናዎች የአፍሪካ ነገዶች ሦስቱን ያካተተው የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ታሪኩ ውስጥ እርስበርሱ ሲጋጭም ሲተባበርም፣ ሲጣላም፣ ሲወዳደርም፣ ሲጋባና ሲተሳሰርም፣ በአንድነት ተሠልፎ ጠላትንና ባንዳን ሲያዋርድና በመስዋዕት ድል ሲዋጅም፣ … አኩሪ ታሪኩን፣ ደማቅና ኀሩጉርና ንብርብር ባህሉን በጋራ የሠራ ትልቅና የአስተሳሰብ ጥልቀት ያለው ሕዝብ ነው።

ለዘመናት በሀገራችን የተፈራረቁት አገዛዞች ደግሞ፣ ይብዛም ይነስም በመላው የሀገሪቱ ሕዝብ ላይ፣ አንዳንዴም ድርብና ድርብርብ በሆነ መልክ፣ ግፍንና ጭቆናን ሲያደርሱ ኖረዋል። ከዚህ ግፍና ጭቆና ራሱን ለማላቀቅ በተለያየ ወቅት፣ አንዱ የኅብረተሰብ ክፍል ወይንም ሌላው፣ ከገዥዎቹ ጋር ትንቅንቅ ያደረገ ሲሆን በተለይም የተማረውና የነቃው ክፍል፣ ሕዝብን ለመታደግ ያደረገው ተጋድሎ ትልቅ ነው።

ይህም ሆኖ ከግማሽ ምዕት-ዓመት በላይ ለመሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶች፤ የመናገር፣ የመጻፍ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመደራጀት፣ ወደፈለገበት ሥፍራ የመንቀሳቀስ፣ በሚመርጠው ሥፍራ የመኖር፣ የንብረቱ ባለቤት የመሆን መብቶች መከበር ቢታገልም፣ እስከዛሬ ድረስ እነዚህን መብቶቹን ሊቀዳጅ አልቻለም። አሁንም ሕዝቡ የመብቶቹን መከበር አምርሮ እየጠየቀ በመላ ሀገሪቱ በየጎዳናው ላይ በጨካኝና በህሊናቢሱ አገዛዝ የፀጥታ ኃይሎችና ልዩ-ገዳይ ኃይሎች ጥይት ግንባሩ እየተፈረከሰና፣ አካላቱ እስከሚደቅ እየተቀጠቀጠ፣ ከባድ መስዋዕት እየከፈለ ይገኛል።

ያለፉት ሁለት ጨቋኝና አስከፊ መንግሥታት በሕዝቡ ትግል ተወግደው በምትካቸው የሕዝቡን ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነት የሚያውቅና የሚያከብር ሥርዓት-መንግሥት ይመሠረታል የሚል ተስፋ ሁለት ጊዜ የተፈጠረ ቢሆንም፣ ሁለቱም ተስፋዎች መክነው በጥቂት መሣርያ አንጋቢዎች ሥልጣን መቆጣጠር ምክንያት የጨለማውና የጭቆናው ዘመን እንዲቀጥል ሆኗል።

በ1991 በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ይመራ የነበረው ጨፍጫፊው የደርግ መንግሥት ሲንኮታኮት፣ በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት ሊመጣና የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ሊመሠረት ይችል ይሆናል ብለው ተስፋ ያደረጉ በርካታ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ነበሩ። የሕዝብን የሥልጣን ምንጭነትና ሉዓላዊነት ሊያረጋግጥ የሚችል የሽግግር ሂደት እውን እንዲሆን በወቅቱ ተደራጅተው ይታገሉ የነበሩትን በርካታ ተቃዋሚ ድርጅቶችን አሰባስቦ በነበረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ብዙ ጥረት አድርጎ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ይሁን እንጂ በጠመንጃ ኃይል ሃገሪቱን የተቆጣጠረው ህወሓት፣ በሽግግር መንግሥት ምሥረታ ሂደት ውስጥ የተለየ አማራጭ የፖለቲካ አስተሳሰብና አቋም ያላቸውን፣ በተለይም ደግሞ በብሄራዊ ደረጃ ተደራጅተው ሲታገሉ የነበሩት የአንድነት ኃይሎችን በማግለል የህወሓት/ኢህአዴግን ጠባብ የፖለቲካ አስተሳሰብ በሃገሪቱ በብቸኛነት እንዲሰፍን አደረገ። በዚህም የተነሳ ገና ከጅምሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጮቹን የማየት ዕድሉን ተነፈገ፤ የሥልጣን ባለቤትነቱንና ሉዓላዊነቱም እንደተገፈፈ ቀረ። ብዙም ሳይቆይ፣ በሽግግር መንግሥቱ ተሳትፈው የነበሩ አንዳንድ የብሄር ድርጅቶች ሳይቀሩ፣ ኢህአዴግ በሚል ህወሓት በጭምብልነት ካሰባሰባቸው በስተቀር፣ ከሽግግር መንግሥቱ ተመነጠሩ። በሽግግሩ ወቅት ሊመሠረቱና ሊጠናከሩ የሚገባቸው የዴሞክራሲና የፍትህ ተቋማት በሙሉ በህወሓት/ኢህአዴግ ብቸኛ የበላይነት ተመሥርተው

የእነሱው አገልጋዮች እንዲሆኑ ተደረጉ። ከዚያ በኋላ ለይስሙላ የተካሄዱት ምርጫዎች በሙሉ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ርትዓዊና ተዓማኒነት የሚኖረው ምርጫ ሊካሄድባቸው የሚችሉትን ሁኔታዎች በሙሉ ስላጠፋ፣ እንደተገመተው ሁሉም ምርጫ-ተብዬዎቹ በአፈናና በማጭበርበር በህወሓት/ኢህአዴግ “አሸናፊነት” ተጠናቀቁ። የህወሓት/ኢህአዴግ መዋቅር ከ"መንግሥታዊ" መዋቅሩ ጎን ለጎን በሃገሪቱ በሙሉ ተዘረጋ። ሁሉም ሥልጣን በህወሓት/ኢህአዴግ የተማከለ ቀጥተኛ እዝና ቁጥጥር ሥር ወደቀ። ፌዴራላዊ ተብሎ የተቋቋመው ሥርዓትም በዚሁ በህወሓት/ ኢህአዴግ ”ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት“ በሚባለው አሠራር ማነቆ ውስጥ ተከረቸመ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉንም ነፃነቶቹን፣ የዜግነት መብቱንም ጭምር ተቀምቶ፣ የጭቆና፣ የግፍና የብዝበዛ ሰለባ እንደሆነ ቀጠለ። የመገናኛ ብዙሃን የጥቃት ሰለባ ሆኑ፣ ነፃ ጋዜጠኞች ታሠሩ፣ ተሰደዱ። የሚያስቡ አዕምሮዎች፣ ለየት ያሉ ሃሳቦችን የሚገልጹ አንደበቶችና የሚጽፉ እጆች ታሠሩ፣ ወይንም ተሰደዱ። ራሱን እንዲያገለግሉት ያቋቋማቸውን ተቋማት በመጠቀም ተፎካካሪዎች የሚሆኑ፣ ሀገራዊ ራዕይ ያላቸው ፓርቲዎችን በሠርጎ-ገቦች እያከፋፈለ አፈራረሰ። ሕጋዊ እየተባሉ የቀጠሉትንም የመሰብሰብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ ሰላማዊ ሠልፍ የመጥራት፣ ነፃ ሆነው የመንቀሳቀስ መብቶቻቸውን ከመጠን በላይ ገደበባቸው። የሃሳብና የዕምነት ነፃነት ታፈነ፣ የሃይማኖት ተቋማት የአገዛዙ አገልጋዮች እንዲሆኑ ተደረገ። አምባገነንነት በሁሉም የሕዝቡ የሕይወትና የእንቅስቅሴ ዘርፎች በመላ የሀገሪቱ ክፍሎች ስፍንን በሚይዝ ደረጃ ሰፈነ።

ሥልጣን ከህወሓት/ኢህአዴግ አባልነት፣ ደጋፊነት፣ ተባባሪነት እንጂ ከሕዝብ ድምፅ የማይመጣ እንዲሆን ስላደረጉ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች በሥልጣን ለመቆየት ታማኝነታቸው ለድርጅቶቻቸውና ለአገዛዙ ብቻ ሆነ። ያፈኑትን ሕዝብ ናቁት፣ ተዛበቱበት። ወደር በማይገኝለት የዝርፊያ፣ የሙስና፣ ዘውገኛና አድሎዓዊ አሠራር ውስጥ ተዘፈቁ። በተለይም "ምርጫ" በተባሉት ትርዒቶች ወቅት ለህወሓት/ኢሕአዴግ አባላት ድምፅ አልሰጡም በሚሏቸው ዜጎች ላይ በዕለት-ተዕለት ኑሯቸው ላይ ጭምር ግፍ ተፈጸመባቸው። ከዩኒቨርስቲና ኮሎጆች ተመርቀው የሚወጡ ወጣቶች የህወሓት/ኢህአዴግ አባል ካልሆኑ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው የማይታሰብ ሆነ። አብዛኛውን ሕዝብ አስገድዶ በመልመል አምስት ለአንድ በሚያያዝ መረብ ጠረነፉት። ፍላጎታቸው በመዋቅሩ አስገድዶ ድምጹን ሁሌም ለነሱ እንዲሰጥ ለማድረግ ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ አባል ያልሆነ ዜጋ

ሁሉ በዓይነቁራኛ የሚታይ ሆነ፣ “ጠላት ሊሆን የሚችል” በሚል ተፈረጀ። የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት በይፋ “ልማታዊ መንግሥት” በሚል የሙክሻ ስሙ ተሸፍኖ በሕዝቡ ጫንቃ ላይ ተጫነ። አማራጭ የፖለቲካ አስተሳሰብ ያለው ሁሉ አንድም “ትምክተኛ” አልያም “ጠባብ ብሄርተኛ” ወይንም "የባዕድ ቅጥረኛ" እየተባለ በጠላትነት ተፈረጀ። የሃይማኖት አስተምሯቸውንና ተቋማቸውን በነፃነት እንዳያካሄዱ የተደረጉት ሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትም በእሥር ቤት ታጎሩ። ኢትዮጵያውያን መብታቸውን ለማስከበር ለዓመታት አስገራሚና ሰላማዊም በሆነ መንገድ እየታገሉ ናቸው። በገዥዎች እየደረሱባቸው ያሉትን አፈናዎች ሁሉ እየተቋቋሙ ትግላቸውን ቀጥለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሀብት የሆነውን የሀገሪቱን መሬት በሙሉ በ“መንግሥት” ማለትም በህወሓት/ኢህአዴግ ቁጥጥር ሥር በማድረግ፣ በመሬቱ ላይ እነሱ አዛዥ ናዛዥ ሆኑ። በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ገበሬውንና አርብቶ-አዳሪውን በግፍ እያፈናቀሉ ለሥራ-አጥነት፣ ለቤት-አልባነት፣ ለእንግልት፣ በአንዳንድ አካባቢም ለስደት ዳረጉት። ይህን በደልና ግፍ ሲቃወምም በግፍ ጨፈጨፉት። በጋምቤላና ሌሎችም አካባቢዎች የዜጎችን መሬት እየነጠቁ ለባዕዳን ተቋራጮች በረጅም ጊዜ ኪራይ (ሊዝ) ነፃ በሚባል ደረጃ ተሰጠ። ሕዝቡ መታፈኑ አንሶት የዘር-ማጥፋት እርምጃ ሰለባ ሆነ።

በአዲስ አበባና በዙሪያው ባሉት ከተማዎች ያሉትን ገበሬዎች መሬት እየቀሙ ዜጎችን በማፈናቀል የህወሓት/ኢህአዴግ አባላት የተነጠቀውን መሬት በመሸጥ በቅጽበት “ልማታዊ” ባለ ሚሊዮንና ባለ ቢሊየን ሃብታሞች ሆኑበት። የተፈናቀሉት ዜጎች ደግሞ ከፊሉ በረንዳ አዳሪዎች ሆኑ። ለርሃብና ለችግር ተጋለጡ። በዜጎች ላይ የሚፈጸመው ግፍና በደል ጎስቋላ ትከሻቸው ከሚችለው በላይ እየተቆለለ መጣ። ስፍሩ ሞልቶ ሊፈስ ቻለ!

ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በአገዛዙ እየደረሱባቸው ያሉትን አፈናዎች ሁሉ እየተቋቋሙ መብታቸውን ለማስከበር ለዓመታት አስገራሚና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ትግላቸውን መቀጠል፣ እንዲሁም በአለፈው አንድ ዓመት በሸዋ፣ በሐረር፣ በባሌ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ በሲዳሞ....ወዘተ ሕዝብ አገዛዙን በጥብቅ መቃወሙና በከፍተኛ ደረጃ እየከፈለ ያለው መስዋዕት፣ ባለፉት ጥቂት ወራትም በጎንደርና በጎጃም አገዛዙን ያንቀጠቀጠ ሕዝባዊ እምቢተኛነት ምንጩ ከላይ ከሽግግር መንግሥት ተብየው እስከ ዛሬ የቀጠለው የአንድ ቡድን ፍጹም አምባገነናዊነትና የፈጠረው አንገሽጋሽ ጭቆና ነው።

ካለፈው ኅዳር ወር ጀምሮ አንድ ዓመቱን ለማስቆጠር የተቃረበው ትውልደ-ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመቃወምና የእኩል ተጠቃሚነትንና የሥልጣን ባለቤትነት በማንሳት በስፋቱና በቀጣይነቱ አርአያነት ያለው እንቅስቃሴ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። በጎንደር የተነሳውና እየተቀጣጠለ፣ አድማሱንም እያሰፋ የመጣው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ በጎንደር ክፍለ-ሀገር የሚገኙትን፣ ወልቃይትን፤ ጠገዴንና ፀለምትን ወደ ትግራይ የተካለሉበትን፣ ተስፋፊነት በመቃወም፣ በሕጋዊ መንገድና በሕዝቡ በተመረጠ ኮሚቴ አማካይነት የተጀመረ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ተገቢ መልስ በማጣቱ የተፈጠረው ብሶትና የፍትኅ እጦት የተነኮሰው ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ እንቅስቃሴውን ለማስቆም ባደረጋቸው እመቃዎች የጎንደርንና የጎጃምን ሕዝብ አስቆጥቶ አነሳሳው። በጠቅላላው የሰብዓዊና የዴሞክራሲ መብት ጥያቄዎችን፣ ሀገራዊ አድማስ የያዙ ጥያቄዎችን፣ እያነሳ እየተጋጋመ ቀጠለ። የጎንደር ሰልፈኞች "የኦሮሞ ወንድሞቻችን ትግል የኛም ነው"፣ "በቀለ ገርባ ይፈታ"፣ "የሙስሊሙ ችግር መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ይፈቱ"፣ "የጋምቤላ፣ የኦሮሞና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በገገርው ነፍሰ-ገዳይ የአግዓዚ ሠራዊት ጥይት የሚፈሰው የወገናችን ደም የኛም ደም ነው" በማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አንድነት አበሰሩ። ዛሬ በተናጠል በተለያየ ወቅትና ሁኔታ የተጀመረው ትግል በገዥዎች ላይ ያነጣጠረ የአንድ ሀገራዊ ትግል ገጽታዎችና አካሎች ሆነዋል። ትውልደ-ኦሮሞ ኢትዮጵያውያንም፣ በተመሳሳይ መልክ፣ እያደረጉት ያለው ትግል፣ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እንደሚደርሰው የመሬት ነጠቃ የመብት ገፈፋ ሁሉ በአዲስ አበባ ዙርያ በገበሬዎች ላይ የሚደርሰውን በደሎችን መነሻ ቢያደርግም፣ ትግሉ ለ25 ዓመት የቆየው ሀገራዊ ጭቆናና ረገጣ የወለደውና በተጨባጭ የተያያዘ መሆኑን በቀጣይ የእምቢተኛነቱ ትግል አሳይቷል። በሁሉም አካባቢዎች የሚደረጉት ትግሎችን አገዛዙ ነጣጥሎ ለማቅረብ ቢሞክርም፣ ሁሉም ሀገራዊና ፀረ-ገዥዎች ትግል አካል መሆናቸውን ከሕዝቡ አብራክ የወጡት ታጋዮች እየገለጡ ይገኛሉ። በመሆኑም እየተደረገ ያለው ትግል በሥልጣን ላይ ያለው ገዥ ቡድን ከሥልጣን እንዲወርድ በማያሻማ መንገድ ጠይቋል።

በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ለሕዝብ ጥያቄና ጩኸት እስካሁን እየሰጠ ያለው ምላሽ በአንድ በኩል ከፋፋይ መርዙን በሕዝብ ውስጥ በመርጨት ሕዝባዊውን ትግል ለመከፋፈልና ለማዳከም መጣር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በመሣሪያ ኃይል ሕዝብን

በማሸበር ትግሉን ለመደፍጠጥ መጣር ነው። ይህም ሆኖ ግን የሕዝቡን እንቢተኝነትና እንቅስቃሴ ለመግታት አልቻለም። እስካሁን ሲወስደው የነበረውን የኃይል እርምጃ በበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል እንዲችል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቢያወጣና ዜጎችን መግደሉንና ማንገላታቱን ቢቀጥልም፣ እራሱን በሕዝብ ደም የበለጠ በመንከር ወደ ከፋ ወንጀል ከመውረድ በተረፈ የሚፈይደው ነገር እንደሌለው ከአዋጁ በኋላም ቢሆን ሕዝባዊ እምቢተኛነቱ መቀጠሉ በግልጥ ያሳያል። በመሣሪያ ኃይል የሕዝብን ደም በማፍሰስ አገዛዙን ለመቀጠል የሚወስደው እርምጃ ደግሞ ህወሓት/ኢህአዴግ በወደፊቷ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ፖለቲካ ድርጅትነት የመቀጠል ተስፋውን እጅግ የሚያመነምነው ይሆናል።

ህወሓት/ኢህአዴግ እውነታውን መረዳት ቢያቅተውም ሀገሪቱን የመግዛት አቅሙም ይሁን በሕዝብ ያለው ታማኝነት ተሟጦ አብቅቷል። ሕዝቡ ዳር እስከ ዳር፣ አናምንህም፣ አንፈልግህም፣ አትገዛንም፣ እያለ ነው። በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ ተንጠልጥሎ ያለው በወታደራዊ ኃይሉ ብቻ ነው። ይህም ኃይል ቢሆን በየቀኑ ውስጣዊ አንድነቱ እየተፍረከረከ በመሄድ ላይ ነው። ስለሆነም ህወሓት/ኢህአዴግ ለራሱ ሲል እንኳን፣ በበለጠ በሕዝብ ደም ራሱን ከማጨማለቅ ተቆጥቦ በአስቸኳይ ሥልጣኑን በመልቀቅ ለሕዝብ ማስረከብ ይኖርበታል። ይህ ባይሆን ግን፣ እስካሁን ተበታትነው ያሉትና በየራሳቸው የሕዝብን ትግል ሲያስተባብሩ የነበሩ እንቅስቃሴዎችና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ኃይላቸውንና ጉልበታቸው በማስተባበርና በማቀናጀት ህወሓት/ኢሕአዴግን ከሥልጣን በማስወገድ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ የሚደረገውን ጉዞ በጋራ መጀመር ግዴታቸው ይሆናል።

በሀገራችን ውስጥ ፍትኅ የታጣበት፣ መብት የተነፈገበት፣ የሕግ የበላይነት በፍጹም የጠፋበት፣ ግፍና መከራ በሕዝብ ላይ የተፈጸመበት የአጭርም የረጅምም ጊዜ ታሪክ ስላለው፣ ከእንግዲህ በጨቋኝ ገዥዎች መገዛትን በፍጹም አይቀበልም። ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ለቀቀ ማለት ደግሞ በአንድ ጀንበር ዘላቂ ሰላምንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊመሠረት ይችላል ማለት አይደለም። የሚቀነሱትን ቀንሶ፣ የሚጨመሩትን ጨምሮና አስተካክሎ፣ የሀገሪቱ ዜጎች የሚስማሙበትና በሕዝብ ይሁንታን ያገኘ ሕገ-መንግሥት ማጽደቅን፣ የሕዝብን አመኔታ የሚያተርፉ ተቋማት ማቋቋምን፣ አድሏዊና ጨቋኝ ሕጎችን ማገድና አዳዲሶችን ማውጣትን፤ ነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒ የሆነ ምርጫ ማድረግን የመሳሰሉ

ሥራዎች የተወሰነ ጊዜ የሚወስዱና የግድ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው። አሁን ካለንበት ወደ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነባት፣ በኩልነትና በአንድነት ሕዝቦቿ የሚኖሩባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የምንወስደው መንገድ ደግሞ በጥንቃቄ የተቀየሰና ማንንም ሳያገል ሁሉንም ያገባኛል የሚል የፖለቲካ ድርጅትና ማኅበረሰብ የሚያሳትፍ መሆን አለበት። ሂደቱ ግልጽና በሕዝብ ሊታመኑ ለሚችሉ የዴሞክራሲና የፍትኅ ተቋማት መሠረት የሚጥል መሆኑ አለበት። ማንም ኃይል ለብቻው ወይንም እራሱንና መሰሎችን ብቻ አሰባስቦ የሚፈጥረው ሂደት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ከእንግዲህ ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህም፣ ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይና ይህንን ጊዜያዊና ታሪካዊ ኃላፊነት ሊወጣ የሚችል <u>ሁሉን አሳታፊ</u> የሽግግር መንግሥት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ በጽኑ ያምናል።

በመሆኑም በኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) በኩል የሽግግሩ ወቅት ምን መምሰል እንዳለበት ያለውን ሃሳብ እንደሚከተለው ያቀርባል።

## ለሽግግር መንግሥት ምሥረታ የሚረዳ የምክክር ጉባዔ ስለመጥራት፣

### <u>የሽግግር መንግሥት፣</u>

የሽግግሩ መንግሥት ባለሦስት ዘርፍ እንዲሆን፣ እነሱም፦

1ኛ/ የሽግግር ምክር ቤት (ሕግ አውጭ)

2ኛ/ የሽግግር አስተዳደር ሕግ አስከባሪ)

3ኛ/ የሽግግር ሕግ ተርጓሚ ናቸው።

### <u>የሽግግር ምክርቤት አመሠራረት፣</u>

በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በፈቃዱ ሥልጣን ለቆ ወይንም በትግል ተወግዶ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም የሚያስችል ሁኔታ ሲመቻች (ዜጎችን መግደልና ማዋከቡ ሲያቆም፣ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ያለቅድመ ሁኔታ ሲፈቱ፣ በፖለቲካ ሁኔታ እንዲሰደዱ የተደረጉና ወደ ሀገራቸው መመለስ የማይችሉ ዜጎች ወደ ሀገራቸው ቢመለሱ የደህንነት ዋስትና ሲያገኙ፣ በ"አሸባሪነት የተፈረጁ"፣ ሕጋዊነት የተከለከሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መሳተፍ ሲችሉ.... ወዘተ) የውጭ ታዛቢዎች ባሉበት በሀገሪቱ

የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሚታወቁና ሌሎችም ህልውናቸው ሊረጋገጥ የሚችል የፖለቲካ ፓርቲዎች/ድርጅቶች እንዲሁም የሚታወቁ የሲቪል ማኅበራት ተወካዮች አንድ ሀገር አቀፍ ጉባዔ በማድረግ በዋና ዋና የሀገሪቱ ጉዳዮችና በሽግግር ምክር ቤት ምሥረታ ላይ በጥሞና ይመክራሉ። ጉባዔው በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ በአቻነት መንፈስ፣ በመቻቻልና በዴሞክራሲያዊ ግንኙነትና በይነግብር ይካሄዳል። ለሽግግር ምክር ቤት ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉትን በነቂስ በመለየትና በመጋበዝ የምክር ቤቱን ምሥረታ ያመቻቻሉ። የሽግግር ምክር ቤቱ ተመሥርቶም ተግባሩን እንዲጀምር ያደርጋሉ።

## የሽግግር ምክር ቤት ተሳትፎን በተመለከተ፣

በሽግግር መንግሥት ምሥረታ ለመሳተፍ ፍላጎት ካላቸው የፖለቲካ ኃይሎች፣ ትግሉን በየአካባቢው ካስተባበሩ “የጎበዝ አለቆች”፣ የማኅበረሰብ ወኪሎች፣ ከሙያ ማኅበር ተጠሪዎች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከታዋቂ ግለሰቦች.... ወዘተ ወኪሎች የሚመሠረት ይሆናል። በሥልጣን ላይ ያለው ህወሓት/ኢህአዴግን በተመለከተ በሽግግር መንግሥቱ በአቻነት ተካፋይ ይሆናል፣ ሆኖም ጭፍጨፋውን ከቀጠለ፣ በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ ተሳታፊነቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፣ ውሳኔውም ለኢትዮጵያዊ ድርጅቶች የሚተው ይሆናል።

## የሽግግር ምክር ቤት ተግባር፣

1. የሀገሪቱን አንድነትና ሉዓላዊነት የሕዝቡንም አንድነት፣ ሰላምና መረጋጋት፣ የሕግ የበላይነትና የዜጎችን እኩልነትና ሰብዓዊ መብቶች ማስከበር፣ በሽግግሩ ወቅት የሚመሠረተው ምክር ቤትም ሆነ የሥራ አስፈጻሚው (የሚኒስትሮች ምክር ቤት) የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነትና ሉዓላዊነት የሚያጠናክር እንጂ በምንም ዓይነት አደጋ ላይ የሚጥል ውሳኔ ለማስተላለፍ ሥልጣን አይኖረውም።
2. የሀገሪቱን የሽግግር መንግሥት ርዕሰ-ብሄርና ምክትል (ፕሬዘዳንትና ምክትል ፕሬዘዳንት) መርጦ ይሾማል፣ ሃላፊነታቸውንና ሥልጣናቸውን ይወስናል። ፕሬዘዳንቱ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ይሆናል (ሁለቱም ተሿሚዎች የፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆኑና ያልነበሩ፣ ለሚቀጥሉት ሁለት የምርጫ ዘመናት ለምንም የፖለቲካ ሥልጣን ለመወዳደር የማይችሉ መሆኑን የሚቀበሉ ቢሆን ይመረጣል)።

3. የሽግግር መንግሥቱ ሥራ አስፈጻሚ (የሚኒስትሮች ምክር ቤት) አባላትን መርጦ ሃላፊነት ይሰጣል፤ ከሥልጣን ማውረድ ሲያስፈልግም ያወርዳል።
4. የምክር ቤቱን አፈ-ጉባዔና ፀሐፊ መርጦ ይሾማል (እነዚህም ሹማምት የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑና ያልነበሩ፣ ለፖለቲካ ሥልጣንም የማይወዳደሩ ቢሆኑ ይመረጣል)።
5. ለሽግግሩ ወቅት ሊያገለግሉ የሚችሉ ሕጎችን ያወጣል።
6. አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገ-መንግሥት ላይ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች ሁሉ ተደርገውበት ለሽግግር ዘመን በቻርተርነት ሊያገለግል ይችላል።
7. ለሽግግሩ ወቅት ችግር ይሆናሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን ሕጎችን ይሽራል።
8. በሽግግሩ ወቅት የሚቋቋሙ ተቋሞችን እንዲመሩ በፕሬዘዳንቱ የሚቀርቡ ዕጩዎችን ያፀድቃል፤ ወይም ይጥላቸዋል።
9. የሽግግር መንግሥቱን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችን ያፀድቃል።
10. በሽግግሩ ወቅት የሀገሪቱን ውስጣዊ የአስተዳደር ቅርጽ በተመለከተ እንደ አስፈላጊነቱ ያስተካክላል።
11. ቅሬታ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችና የአገሪቱ ክፍሎች በሚመድባቸው ወኪሎች አማካኝነት ያነጋግራል። በሽግግሩ ዘመን ሊፈቱ የሚችሉትን ችግሮች በድምፅ ብልጫ እየወሰነ ይፈታል።
12. ሥራ አስፈጻሚው የተሰጠውን አደራ በአግባቡ ማከናወኑን ይከታተላል።

<u>የሽግግር ሥራ አስፈጻሚ (የሚኒስትሮች ምክር ቤት)፤</u>

1. የሥራ አስፈጻሚው አካል (የሚኒስትሮች ምክር ቤት) የፖሊቲካ ድርጅቶችና በሀገሪቱ ውስጥ እውቅ የሆኑ ባለሙያዎችን ባካተተ መልክ ይዋቀራል።
2. ተጠሪነቱ ለሽግግር ምክር ቤቱ ይሆናል።
3. የሀገሪቱን ድንበሮች ይጠብቃል።
4. የሽግግሩ ወቅት መስተዳድር የቀን ተቀን ሀገሪቱን የማስተዳደር ሥራውን ከመሥራት ባሻገር፤ ተገቢውን ቅድሚያና ትኩረት ሰጥቶ በሀገሪቱ ውስጥ፣ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊው ሽግግርና ምርጫ የሚያስፈልጉት ዝግጅቶች ሁሉ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋል።

5. የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ያደርጋል፣ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉና ሳይገደቡ ተግባራዊ መሆናቸውን በተግባር ይከታተላል።
6. የሙያ ብቃት ያላቸው ነፃና ገለልተኛ ዜጎችን ለምርጫ ቦርድ አባልነት ዕጩ በማድረግ ለምክር ቤቱ ያቀርባል። የምርጫ ቦርዱ ተልዕኮ እንዲሳካ አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ ያደርጋል።
7. ብሄራዊ የመከላከያ ሠራዊትና የደህንነት ተቋሞች ሁሉ የአገራቸውን ድንበር መጠበቃቸውን፣ የሕዝቡን ሰላማዊ ኑሮ መከታተላቸውንና ሙሉ በሙሉ ከፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት እንዲላቀቁና የሀገሪቱን ብዙሃዊነት የሚያንፀባርቅ ይዞታ ያላቸው ተቋማት እንዲሆን ያደርጋል።
8. የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በፍትኅ የተመሠረተ፣ ያለ አድልዖ ለሁሉም ፓርቲዎችና ለሽግግር መንግሥቱ ማገልገላቸውን ያረጋግጣል።
9. በረሃብ ለተጠቁ ወገኖቻችን ልዩ ትኩረት በመስጠት ይሠራል።
10. ከውጭ ወደ አገራችን በተስፋ የሚመለሱ ዜጎቻችን እንዳይጉላሉና ለችግር እንዳይጋለጡ የማቋቋሚያና የዕርዳታ ክፍል ይመሠርታል።
11. የአገሪቱ የውጭ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መቀጠሉን ያረጋግጣል።
12. የሽግግር መንግሥቱን የሚመሩ ሚኒስትሮችና ረዳቶቻቸው በሙያ፤ በልምድና ብሄረሰብን፤ ፆታንና ሃይማኖት ተዋፅዖ ስብጥርን ግብዓት ባደረገ መንገድ መሰየማቸውን ያረጋግጣል።

13. ሀገሪቱን ወደ ቋሚ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር እንዲቻል፦
    ሀ) ሕገ-መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ከሕግ ባለሞያዎች፣ ከታሪክና ከፖለቲካ ሊቃውንት፣ ከዋና ዋና ሃይማኖቶች ተቋማት ተወካዮች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሴቶች ማኅበር ተወካዮች፣ ከወጣቶች ማኅበራት ተወካዮች ተውጣጥቶ እንዲቋቋም ያደርጋል።
    ለ) መመሪያቸውንና የኮሚሽኑ አባላትንም በሽግግር ምክር ቤት እንዲፀድቅ ያደረጋል።
    ሐ) የተቋቋመው አርቃቂ ኮሚሽን የህወሓት/ኢህአዴግን "ሕገ-መንግሥት" እንደ ረቂቅ ሊጠቀምበት ይችላል።

መ) ኮሚሽኑ በመቻቻል፣ በሰጥቶ መቀበልና እጅግ ሰፊ የሀገሪቱን ማኅበረሰብ ፍላጎት ለማንጸባረቅ በሚያስችል መንገድ፣ በተቻለ መጠንም የሁሉንም የኅብረተሰቡን ክፍሎች ድምፅ ያካተተና አወንታዊነትንም ያገኘ ግልጽ የሕገ-መንግሥት የማርቀቅን ሂደት ተግባራዊ ያደርጋል።

ሠ) በሚዘጋጀው ረቂቅ ሠነድ ላይ ስምምነት ላይ ሲደረስ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላ የሚወያይበትንና አዲሱን ሕገ-መንግሥት የሚያፀድቅበትን መንገድ በምክር ቤቱ መመሪያዎች መሠረት ያዘጋጃል።

14. መስተዳድሩ፣ በምክር ቤቱ አፀድቆ፣ ከሃይማኖት መሪዎች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎችና ከሲቪክ ድርጅቶች የተዋቀረ ሁለተኛ ኮሚሽን አቋቁሞ የብሄራዊ እርቅ ውይይት ያካሂዳል። የዚህንም ኮሚሽን መመሪያ በምክር ቤቱ ያፀድቃል።

15. የሙስና መርማሪ ኮሚሽን፣ ቀድሞ በሚያወጣው መሥፈርት መሠረት፣ ያቋቁማል፣ የኮሚሽኑ ዕጩ አባላትን መርጦ በምክር ቤቱ ያፀድቃል። መመሪያቸውንም አውጥቶ ያፀድቃል። ምርመራ እንዲያካሂዱ ያደርጋል፣ ይተባበራቸዋል፣ ውጤቶችን ይመዘግባል። የሚመለሱ ንብረቶችን ወደሚመለከተው ክፍል በሚወሰነው መሠረት ገቢ ያደርጋል። በሽግግሩ ወቅት ያልተገባደዱና ወደፊት ክትትል የሚጠይቁ ጉዳዮችን ለቋሚ መንግሥት ያስተላልፋል።

16. በሀገሪቱ ውስጥ የተጀመሩ ማናቸውንም መሠረተ-ልማቶች ለምሳሌ እንደ አባይ ግድብ የመሳሰሉትንና ሌሎችንም፣ በሕዝብ ኑሮና ጤንነት ላይ ጉዳት እስካላስከተሉ ድረስ፣ በሽግግሩ ዘመን እንዲቀጥሉ ያደርጋል።

17. የሽግግር መንግሥቱ ዕድሜ ሦስት ዓመት ይሆናል። ሦስተኛ ዓመቱ የምርጫ ዘመቻና በፓርቲዎች መካከል ክርክሮች የሚካሄዱበት ወቅት ነው። የምርጫ ቦርድ የምርጫውን ዝርዝር ጉዳዮች ይወስናል፤ ያስታውቃል። መንግሥት ተረካቢ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ሥልጣን እንደተረከቡ የሽግግር መንግሥቱ ዘመን ያበቃል።

18. አመፅ፤ የዘር መነሳሳትና ፀረ-ሽግግር መንግሥት ትጥቃዊ እንቅስቃሴ የተከለከለ ይሆናል።

**<u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አመሠራረትን በተመለከተ፣</u>**

በሀገራችን ተንሰራፍቶ ያለውን የፍትኅ መጥፋትና መዛባት፣ የሕግ የበላይነት መጥፋትና ሕዝብ በፍትኅ አካላት ላይ ያለው አመኔታ መሸርሸርን ግምት ውስጥ በማስገባትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ ተዓማኒነት ያለው የፍትኅ አካላትን መሠረት ለመጣል ለሽግግሩ ወቅት የዳኞች አስተዳደር በልዩ ሁኔታ እንዲቋቋም ሀሳብ እናቀርባለን።

በዚህም መሠረት፣ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አባላት የሽግግር ምክር ቤቱ በሚጠራው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች በሙሉ ጉባዔ ይመረጣል። የዳኞች አስተዳደርም በነፃነት ይሠራል።

-----/////-----